# በህወሃት ሤራ የተከናወነው የሱዳን ወረራ በኦታዋ ሰላማዊ ስልፍ ተወገዘ




የካናዳ ዋና ከተማ በሆነችው በኦታዋ ከተለያዩ ከተሞች የተሰባሰቡ ኢትዮጵያውያን በምዕራብ ኢትዮጵያ በሱዳን ወታደሮች የተደረገውን ድንበር ዘለል ወረራ በመቃወም ባለፈው ዓርብ፤ ግንቦት 15፣ 2000 ዓ.ም ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው ውለዋል። ይህ ከቶሮንቶና ሞንትርያል ከተሞች በመጡና በኦታዋ ኗሪ በሆኑት ኢትዮጵያውያን ተሣትፎ የተደረገው ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ፣ የሱዳን ወታደሮች ድንበር አቋርጠው ላደረጉት ጥቃት ዋነኛ ምክንያትና ተባባሪ የሆነውን የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ሤራም አጥብቀው አውግዘዋል። ለሃገር ሉዓላዊነት ደንታ የሌለው የመለስ ዜናዊ አምባገነን ቡድን ዛሬም እንደገና ሃገሪቱን ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅሙ ሲል ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱ ታሪክ ምህረት ሊያደርግለት የማይችል ክህደት መሆኑን የሰላማዊ ሰልፈኛው በቁጭት ባሰማውና በጽሁፍም በያዘው መፈክሩ ገልጿል።

በሱዳን ኤምባሲ በር ላይ፤ የአካባቢው ነዋሪ እስኪገረምና የከተማው ፖሊሶችም መጥተው መስተንግዶ እስኪሰጡ ድረስ፤ ሠፈሩን ያናወጠው ሰልፈኛ "በአጼ ዮሐንስ ደምና በጀግኖች አባቶቻችን አጥንት የተጠበቀው ድንበራችን ለሱዳን አይሸጥም፣ ሱዳን ወረራውን በማቆም ባስቸኳይ ይውጣ፣ ተጠልፈው የተወሰዱ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ባስቸኳይ ይፈቱ....ወዘተ፤ የሚሉ መፈክሮችን አሰምቷል።




ከዚያም ሠልፉን ባስተባበረው ወገን በተጻፈና ለካናዳ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ተጽፎ በተሰጠ ደብዳቤም፣ በ1997 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝብ በድምጹ አምባገነናዊ አገዛዙን እንደሻረና ይህንን ውሳኔ-ህዝብ ያልተቀበለው የመለሰ መንግሥት ግን ምርጫውን ያሸነፉ ተመራጮችን እስር ቤት አጉሮ በጠመንጃ ኃይል ሥልጣኑን እንደያዘ መቀጠሉንና ይህም ከሃዲ መንግሥት ሥልጣኑን ለማቆየት እስከረዳው ድረስ የሃገሪቱ ዳር ድንበር መደፈር አንዳችም ደንታ የማይሰጠው መሆኑን አስረድተዋል። ይህ ኃላፊነት የጎደለው ጎጠኛ መንግሥትም አስተዳድራታለሁ የሚላትን አገር ዳር ድንበር አስደፍሮና የኢትዮጵያን መሬት ገምሶ ለሱዳን እንዲቸር ካበቁት ምክንያቶች አንዱ የሱዳን መንግሥት በምላሹ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ጥገኞችን መብት እንዲነፍግ፤ ተቃዋሚ የሚባሉትን ወገኖችም ካሁን በፊት እንዳደረገው በጥብቅ እንዲቆጣጠርለትና ለመለስም አሳልፎ እንዲሰጥ ታስቦ የተደረገ እንደሆነ አጽንዖት በመስጠት ይሄው ደብዳቤ ይገልጻል።

በመጨረሻም፤ የካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ያላቸውን ዲፕሎማሲያዊ ኃይል በመጠቀም የሱዳን ወታደሮች ከኢትዮጵያ ምድር ባስቸኳይ ለቀው እንዲወጡ፤ ታፍነው የተወሰዱት ኢትዮጵያውያን እንዲፈቱ እንዲያደርጉና በኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ላይ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ግድያ፣ እንግልትና የሰብዓዊ መብት ረገጣም የሚከታተልና የሚዘግብ የመልዕክተኛ ቡድን ወደ ሥፍራው እንዲልኩ ጠይቀዋል።

ይህንንም ሰላማዊ ሠልፍ ቮይስ ኦፍ አሜሪካ የአማርኛው ክፍልና የህብረት ራዲዮ ተከታትለው ለህዝብ መዘገባቸው ታውቋል።

**የሰላማዊ ሠልፉ አስተባባሪ ኮሚቴ**